+ ● ■ × Let's make this
× ● + / our healthiest
G E N V generation
■ • ■ / ever

murdoch children's research institute

# GenV Parent/Guardian Information Statement
# ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የመረጃ ቃል

## 1. ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ለምን?

የጄነሬሽን ቪክቶርያ (GenV) አጭር መጠሪያ ሲሆን፣ በመላው ከፍለ አገር የሚካሄድ የምርምር መርሃ ግብር ነው። የመላውን ትውልድ ጤንነት እና ደህንነት ሙሉ ስእል ይሰጣል።

ለሁለት ዓመት ለሚቆይ፣ በቪክቶሪያ ለሚወለዱ ሁሉም ሕጻናት ኢንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። ማንም ይሁኑ፣ የትም ይኑሩ፣ ሁሉንም ወላጆች እና ሕጻናቶች ማካተት እንፈልጋለን። ማንኛውም ቤተሰብ ተፈላጊ ነው - የእርስዎንም ጨምሮ።

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ሌሎች አገልግሎቶች ያሰባሰቡትን ዳታ እርስዎ ከሚሰጡን ጋር ያቀላቅላል። ይህ ማለት ከጊዜዎ ጥቂት ሊወስድ ይችላል። ወደፊት የሚሠሩ ጥናቶች ውስብስብ ለሆኑ የጤና እና የደህንነት ጥያቄዎች ከዛሬ በተሻለ ፍጥነት መልስ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

ዛሬ ልጆች እና ቤተሰቦች የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለመከላከል፣ ቀድሞ ለማወቅ እና ለማከም ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ይረዳል ብለን ተስፋ እናደጋለን። ለሁሉም ያለወቅቱ መወለድ፣ አለርጂ እና የአእምሮ በሽታ ችግሮች ቀንሰው ማየትን እንፍፈልጋለን።

የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) አካል በመሆን፣ ለሁሉም ቤተሰቦች የተሻለ የወደፊት እድል ለመፍጠር ይረዳሉ።

## 2. የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) አካል እንዲሆኑ ግብዣ

እርስዎና ልጅዎ በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) እንዲሳተፉ ጋብዘንዎታል። በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ለመሳተፍ፣ በመጨረሻ ላይ የሚገኘውን የስምምነት ቅጽ መፈረም ይኖርብዎታል። የዚህን ዶኩመንት እና የስምምነት ቅጽ ግልባጭ እንዲያስቀሩት ይሰጥዎታል ። እንዲሁም በዚህ ድረገጽ ላይ ያገኙታል [www.genv.org.au](http://www.genv.org.au)።

ከመወሰንዎ በፊት፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ለምን እንደሚደረግ እና ምን እንደሚጨምር እንዲገባዎት ያስፈልጋል። አላማችን የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የሠራተኞች አባል ልጅዎ እንደተወለደ በሆስፒታል እንዲነበኙዎት ለማድረግ ነው - ስለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በግል ይነግሩዎታል። እባክዎን የፈለጉትን ያህል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

በተጨማሪም፣ ይህንን ዶኩመንት በማንበብ ወይም ቀጥሎ ባለው ድረገጽ ላይ የሚገኘውን ቪዲዮ በመመልከት ስለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) መማር ይችላሉ [www.genv.org.au](http://www.genv.org.au)። በተጨማሪም፣ በኢሜል [genv@mcri.edu.au](mailto:genv@mcri.edu.au) ወይም በነፃ ስልክ 1800 436 888 (1800 GEN VVV) ሊገናኙን ይችላሉ። ጥያቄዎችዎን ለመመለስ ደስተኞች ነን።

## 3. ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ማለት ምን ማለት ነው?

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በአውስትራሊያ ከዚህ በፊት በጭራሽ ተደርጎ የማያውቅ በጣም ትልቁ የጥናት መርሃ ግብር ነው። ልጆች እንዴት እንደሚያድጉና እንደሚጎለብቱ፣ ሰዎች እንዴት እንዲሚያረጁ እና ጤና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እንደሚለወጥ በግልጽ የሚያሳይ ነው። ለተመራማሪዎች የግንባታ ብሎኬቶችን ይፈጥራል፣ ማህበረሰቦች እና ፖሊሲ አውጪዎች አንድ ላይ በመሆን ጤና እና ደህንነት እንዲያሻሽሉ ይረዳል። ወደ ተሻለና ደህንነቱ የተጠበቀ እንክብካቤ እንደሚያመራ ተስፋችን ነው፣ እንዲሁም ልጆቻችን እና ቤተሰቦች የሚጋፈጧቸውን አንዳንድ በጣም አስፈላጊ ጥያቄዎችን ይመልሳል። ከሁለት ዓመት በኋላ፣ በመላው ቪክቶሪያ 160,000 ህጻናትን እና ወላጆቻቸውን በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) እንጋብዛለን።

ፈቃደኛ ሆነው፣ ከጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ጋር ሲፈራረሙ፣ ከእርስዎ እና ከልጅዎ አንዳንድ መረጃዎች እና የምራቅ ናሙና እንሰበስባለን፣ ከዛም ልጅዎ እያደገ ሲሄድ የሚቀጥል ይሆናል። ከእዛም፣ በእርስዎ ፈቃድ፣ አገልግሎቶች እስከአሁን በተለምዶ ሥራቸው የሰበሰቡትን መረጃዎች እና ናሙናዎች እንጨምራለን። መረጃዎቹ ለወደፊት ምርምር ጥቅም ላይ እንዲውሉ በተጠበቀ ዳታቤዝ ውስጥ ይካተታል። ውጤቶቹ፣ እንዴት እንደምናክም፣ ለመተንበይ እና ችግሮችን ለመከላከል ይረዳል። በተጨማሪም የፖሊሲ አውጪዎች የቪክቶሪያን ቤተሰቦች ለመደገፍ ጥሩ ውሳኔዎች እንዲያደርጉ ይረዳል።

ይህ ማለት፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ከእርስዎ ጥቂት ጥረት ብቻ ይፈልጋል፣ ነገር ግን ለቤተሰቦች ትርጉም ያለው ለውጥ

ይፈጥራል። ለብዙ ዓመታት ስለቤተሰብ ጤና እና ደህንነት ለማጥናት ተስፋ እንደርጋለን።

እንደ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ያሉ መርሃ ግብሮች በአሁኑ ወቅት አዛውንቶችን በዓለም ዙሪያ እየረዱ ነው። ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) እነዚህን ጥቅሞች ለልጆች እና ለጎልማሳ ቪክቶሪያኖች ለመፍጠር ተስፋ እናደርጋለን።

## 4. ጄነሬሽን ቪክቶሪያ(GenV) የሚያካሂደው ማን ነው?

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የሚመራው ከሜልበርን የልጆች ግቢ ነው (የመርዶክ የልጆች የምርምር ኢንስቲቲዩት፣ የሮያል የልጆች ሆስፒታል እና የሜልበርን ዩኒቨርሲቲ፣ በሮያል የልጆች ሆስፒታል ፋውንዴሽን ይደገፋል)። የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከቪክቶሪያ መንግሥት እና ከፖል ራምዜይ ፋውንዴሽን ነው። የሚከተሉት ድጋፍ ይደረግለታል፡

- በእርስዎ የማወላጃ እና የአካባቢ የልጆች ሆስፒታሎች
- የቪክቶሪያ ዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ድርጅቶች
- በቪክቶሪያ፣ አውስትራሊያ እና በዓለም ዙሪያ የሚገኙ መሪ ባለሙያዎች
- ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ለማቀድ የረዱት፣ የአካባቢ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች።

የሳይንቲፊክ ዳይሬክተሯ ፕሮፌሰር መሊሳ ዌክ፣ ፔዲያትሪሺያን - የልጆች ሃኪም ። ስለእርሷ እና ስለቀሪው የቡድኑ አባላት እዚህ ላይ ማንበብ ይችላሉ እዚህ.

## 5. ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) እንድንቀላቀል ለምን ጠየቁን?

ከሁለት ዓመታት በላይ፣ በቪክቶሪያ የተወለዱ ሁሉም ህጻናቶች እና ቤተሰቦቻቸው፣ በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። የተጋበዙበት ምክንያት ልጅዎ በዚህ ጊዜ ቪክቶሪያ ውስጥ ስለተወለደ ነው።

## 6. ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በምን ዙሪያ ይሰራል?

የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ቡድን ልጅዎ እንደተወለደ ይጎበኝዎታል ወይም ያገኝዎታል - አብዛኛውን ጊዜ በሆስፒታል ውስጥ ነው። ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በሁኔታዎች ለሚቀላቀሉት ሰዎች በተቻለ መጠን እንዲቆዩ ያልማል። ጉብኝቱ በግምት ከ15-20 ደቂቃዎች ይወስዳል። ስለመርሃ ግብሩ እናስረዳለን፣ ከልጅዎ ጋር ሆነው ለመሳተፍ ፈቃደኛ እንደሆኑ እንጠይቅዎታለን፣ አጭር መጠይቅ እንሰጥዎታለን እናም እቤትዎ ሆነው የሚጠቀሙበት የምራቅ ጥራጊ የናሙና ኪት እና እቤትዎ ሆነው የሚጠቀሙበት ናሙና እንሰጥዎታለን። በተጨማሪ ስለእነዚህ ስለእያንድአንዱ ከታች ይመልከቱ። የሚችል ከሆነ፣ ሌላውን የልጁን ወላጅ እንጋብዛለን። ከእዚህ በኋላ፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) አብዛኛውን ጊዜ የሚገናኙዎት በኢሜል ወይም በአጭር መልእክት ነው።

**በመካፈልዎ፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የሚከተሉትን እንዲያደርግ ተስማምተዋል፡**

**(1) ያሉትን መረጃዎች እና ናሙናዎች አንድ ላይ ማድረግ። እሱም የሚከተሉትን ያካትታል፡**

- ልጅዎ ከመወለዱ በፊት እና ለወደፊት፣ አገልግሎቶች ከእርስዎ እና ከልጅዎ የሰበሰቡትን መረጃ። እሱም የእርስዎ እና የልጅዎ የአካል እና የአእምሮ ጤና፣ የትምህርት እና የማህበራዊ ሬኮርዶች እና አገልግሎቶች፣ እንዲሁም የትውልድ እና የሞት መረጃዎችን ያካትታል። ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) እነዚህን ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች እና ከመዋእለ ህፃናት እና ከሆስፒታሎች፣ ከዶክተሮች እና ከሌላ አገልግሎት ሰጪዎች ያገኛል።
- ተዛማጅ የሆኑ የጎረቤት መረጃዎች፣ እንደ አየር መበከል እና ቤትዎ አካባቢ ያሉትን የልጆች እንክብካቤ አገልግሎቶች ያሉትን ያካትታል።
- የጤና አገልግሎቶች ከእርስዎ ልጅዎ ከመወለዱ በፊት እና ወደፊት ከእርስዎ ወይም ከልጅዎ የሰበሰቡትን ናሙናዎች፣ የደም ወይም የሽንት ምረመራ ወይም የምራቅ ምርመራ ሲያደርጉ፣ ቀሪው ናሙና ለወደፊት ለቀናት ፣ ለወራት ወይም ለዓመታት ይቀመጣል። ወደ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በማዛወር በሚገባ እንከባከባቸዋለን። ናሙናዎቹ በርካታ ቤተሰቦችን ለመጥቀም እንደገና ለጥናት በጥቅም ላይ ይውላሉ።

*ስለምንሰበስበው በተጨማሪ ለማንበብ፣ ከማን እንደምንሰበስበው እና እንዴት እንደምንጠቀምበት እዚህ ላይ ይመልከቱ www.genv.org.au/for-parents።*

**(2) እቤት የሚውስዱት የናሙና ኪት ይሰጥዎታል።** የሚስማሙ ከሆነ፣ አንዱን ወይም ሁለቱንም ናሙናዎች ሰብስበው ለእኛ በፖስታ ይላኩልን። በጉብኝታችን ወይም በግንኙነታችን በስተመጨረሻ ሁሉንም እናስረዳዎታለን። ፓኬቱ የሚከተሉትን ይይዛል፡

- የሽንት ጨርቅ ጥራጊ የናሙና መሰብሰቢያ ኪት - ጄንቪን (GenV) ከተቀላቀሉ በኋላ በቶሎ ከልጅዎ የሽንት

ጨርቅ ላይ የካካ ናሙና ይወስዳሉ። በጉብኝታችን ወይም በግንኙነታችን በስተመጨረሻ ሁሉንም እናስረዳዎታለን። ናሙናው የሆድ እቃ ጤንነት እንዴት እንደሚጎዳ ለመማር ጥቅም ላይ ይውላል። *ስለ የሽንት ጨርቅ የናሙና መውሰጃ በተጨማሪ [እዚህ] ያንብቡ።*

- የጡት ወተት ኪት - ጡት የሚያጠቡ ወይም የሚያልቡ ከሆነ፣ ጄን ቪን (GenV) ሲቀላቀሉ የጡት ወተትዎን አንድ የሻይ ማንኪያ ያህል ይሰብስቡ። ይህ ስለህፃናት እና የወላጆች ጤንነት እንዲሁም ስለአመጋገብ የሚደረገውን ጥናት ይደግፋል። *ስለጡት ወተት ናሙና ተጨማሪ [እዚህ] ያንብቡ።*

**(3) አልፎ አልፎ የእርስዎን እና የልጅዎን ጤና፣ እድገት እና ደህንነት ለመከታተል አጭር ግንኙነት እንደርጋለን።** ለምሳሌ፣ በዓመት ለበርካታ ጊዜያት አጭር መልእክት ወይም ኢሜል ወይም ልጅዎ እድሜው ሲጨምር ፊት ለፊት መግኘት ልንልክልዎት እንችላለን። በዚያን ጊዜ ለመሳትፍ ወይም ላለመሳተፍ መወሰን ይችላሉ።

**(4) ናሙናዎችን እና መረጃዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ማግኘት፣ ማስቀመጥ እና መጠቀም።** ለጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የሰጧቸውን መረጃዎች ከላይ እንዳዩአቸው አይነት አገልግሎቶች ጋር እንዲቀናጁ እናደርጋለን። ናሙናዎቹ እና መረጃዎቹ የስነ ምግባር ፈቃድ ላገኘና ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በሚያረኩ መንገዶች ለወደፊት ምርምር ጥቅም ላይ ይውላሉ። *[ዳታዎችን ማከማቸትን በተመለከተ ክፍል 13 እና 14 ይመልከቱ]።*

**(5) እርስዎ እና ልጅዎ በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ውስጥ መሆናችሁን ለአገልግሎቶች ይንገሩ።**

**ለሚከተሉት ስምምነትዎን ለመስጠት ወይም ላለመስጠት መምረጥ ይችላሉ:**

**(6) ከጉንጭ ውስጥ ተወስዶ የሚደረግ የእርስዎ እና የልጅዎ የምራቅ ምርመራ።** የምራቅ ምርመራ የተለያዩ የባዮሎጂካል ምርምሮችን ይደግፋል፣ የጄነቲክ ምርምሮችን ጭምር። *በተጨማሪ፣ ስለ ምራቅ ምርመራዎች እዚህ ላይ ያንብቡ [እዚህ].*

**(7) የናሙናዎች ጥቅም (ለምሳሌ፣ የምራቅ ምርመራ ወይም አዲስ የተወለደ ልጅ የማጣሪያ ካርድ) ለጄነቲክ ምርምር፣ ጂን ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር እንዴት አድርጎ እንደሚሠራና ጤና እና እድገት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያደርግ።** ይህ ተመራማሪዎች አዲስ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይረዳቸዋል፣ ለምሳሌ፣ ሁኔታዎች እና አስጊ ነገሮች ከወላጆች ወደ ልጆች እንዳይተላለፉ ለማድረግ። ወደፊት፣ አዲስ ቴክኖሎጂ ሌላ አይነት ምርመራ ሊፈቅድ ይችል ይሆናል። *በተጨማሪ ስለጂን [እዚህ] ያንብቡ።*

### *ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በእኔ ፈቃድ ምን አይነት መረጃዎችን ያገኛል?*

አንድ አንድ ምሳሌዎች፡

- የአካል እና የአእምሮ ጤና፡ ለምሳሌ ሜዲኬር፣ የሆስፒታል ሬከርዶች፣ የዲጂታል ስካን ግልባጮች እንደ አልትራሳውንን፣ ስለእርግዝናዎ የተሰበሰቡ መረጃዎች
- ትምህርት፡ ለምሳሌ በትምህርት ቤት አገር አቀፍ መሰረተ ትምህርት እና የቁጥር ግምገማ፣ ልጅዎ የሚሳተፍ ከሆነ
- ማህበራዊ፡ ለምሳሌ፣ ስንኩልነት፣ የልጅ እንክብካቤ ድጋፍ/በጎ አድራጎት፣ ቤት፣ ፍትህ
- ስለጎረቤቶችዎ አጠቃላይ መረጃ፡ ለምሳሌ የልጆች እንክብካቤ ቦታ፣ የአየር ብክለት።

*ስለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የዳታ መገኛ ቦታዎች በተጨማሪ [እዚህ] ያንብቡ እና በየዓመቱ የምናገኛቸውን ምንጮች ከ [www.genv.org.au] ይመልከቱ።*

### *በእኔ ፈቃድ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ምን አይነት ናሙናዎችን ነው በየጊዜው የሚያገኘው?*

ናሙናዎቹ የሚያካትቱት፡

- በእርግዝናዎ በ10-12ኛው ሳምንት ወቅት ተደርጎ ሊሆን በሚችለው የመለያ የደም ምርመምራ - ልጅዎን ለአንድ አንድ ሁኔታዎች መመርመር። ስለ 10 ሳምንት የመለያ ምርመራ በተጨማሪ ያንብቡ [እዚህ]።
- የደም ናሙና አዲስ ከተወለደው ልጅዎ የደም ናሙና የማጣሪያ ካርድ (ከተረከዙ ላይ ከተወሰደው ደም) - ሊታከም ስለሚችል ልዩ ሁኔታዎች ለመፈተሽ። አውስትራሊያ ከተወለዱ፣ የሚኖር ከሆነ የእርስዎን የግል ካርድ ማግኘት እንፈልጋለን። አዲስ ስለተወለዱ ልጆች የማጣሪያ ካርድ በተጨማሪ [እዚህ] ያንብቡ።
- በእርግዝናዎ ወቅት ሌሎች በየጊዜው ሰጥተዋቸው የነበሩ ናሙናዎች እና ወደፊት ለመሄድ እርስዎም ሆኑ ልጅዎ ሰጥተዋቸው ሊሆኑ የሚችሉ ናሙናዎች።

*ስለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በየጊዜ ለሚሰጡ ናሙናዎች [እዚህ](#) ያንብቡ እና በየዓመቱ የምናገኘውን ናሙና እዚህ ላይ ይመልከቱ [www.genv.org.au](http://www.genv.org.au)።*

### *ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ሲያገኝኝ ምን ይሆናል?*

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በግምት በዓመት አራት ጊዜ፣ እርስዎ እና ልጅዎ በምን ሁኔታ ላይ እንዳላችሁ እንድትገልጹ ይጋብዛችኋል። ግንኙነቱ ከ3 እስከ 20 ደቂቃዎች ሊወስድ ይችላል። በየጊዜው መጠይቆቹን መሙላት ወይም ያለመሙላት ከፈለጉ መወሰን ይችላሉ። ግንኙነቶቹ እነዚህን ያካትታሉ፡

- የሚሞሏቸው አጫጭር መጠይቆች እና ወቅታዊ መግለጫዎች።
- የጤና እና የእድገት መለኪያዎች። እነዚህም እንደ የአእምሮ ጨዋታዎች፣ ለአደጉ ልጆች መነጋገርን እና የልብ ምት መጠንን ይሸፍናል። ለምሳሌ፣ ምንአለባትም የልጅዎን አጭር ቪዲዮ ያነሳሉ ወይም እርስዎ ወይም ልጅዎ ስልክን በመሳሰሉ የኤሌትሮኒክ መሳሪያ ላይ ጨዋታ ሊጫወቱ ይችላሉ። በተቻለ መጠን አጭር እና የሚያስደስቱ ናቸው። ስለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) መለኪያዎች በተጨማሪ [እዚህ](#) ያንብቡ ።
- ከጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ዜናዎች እና ወቅታዊ መግለጫዎች። ይህም ከጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ጋር በጥናቶች ላይ ለመሥራት ግብዣዎችንም ይጨመራል።

*ከጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ጋር ጥናቶች እና አብሮ መስራትን በተመለከተ  በተጨማሪ [እዚህ](#) ያንብቡ።*

### *ልጆች ካደጉ በኋላ የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ግምገማ እንዴት ይሆናል?*

አንዳንድ የጤና እና የእድገት መለኪያዎች  ፊት ለፊት ብቻ ሊደረጉ ይችላሉ። ሁሉንም የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ልጆች ከአደጉ በኋላ እንደምንጎበኛቸው ተስፋ እናደርጋለን፣ ለምስሌ ትምህርት ሲጀምሩ። እነዚህን ጉብኝቶች ገና አላዘጋጀንም። በወቅቱ ለመሳተፍ ወይም ላለመሳተፍ መወሰን ይችላሉ። ልናገኝዎ እስከቻልን ድረስ መረጃ በሚገባ እንዲያገኙ እናደርጋለን። *ስለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ጉብኝት በተጨማሪ [እዚህ](#) ያንብቡ።*

### *ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ለአገልግሎቶች ልጄና እኔ በየጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ወስጥ መሆናችንን መስጠት ለምን አስፈለገ?*

ሌሎች አገልግሎቶችም መደበኛውን ጉብኝትዎን በሚያደርጉበት ጊዜ ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) አጫጭር ቃለ መጠይቆችን ወይም ግምገማዎችን በማድረግ ሊረዱ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የልጅዎ ነርስ ለልጅዎ ተጨማሪ የአይን ምርመራ ለማድረግ፣ አስተያየት ለመስጠት እና ውጤቱን ለመመዝገብ  ልትጠይቅዎ ትችላለች። አንድ አንድ ጊዜ አድራሻ ሊለውጡ ወይም የግንኙነት ዝርዝርዎን ሊለውጡ ይችሉ ይሆናል። አገልግሎቶች ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) አዲሱን የአድራሻዎን ዝርዝር ወቅታዊ እንዲሆን ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ለመውጣት ማሰብዎን ካላወቅን። አገልግሎቶች የጤና እና የትምህርት አቅራቢዎችን እንደ የእናት እና የልጅ የጤና ነርስ፣ ዶክተርዎ፣ ሆስፒታሎች፣ ሜዲኬር፣ ሴንተርሊንክ፣ መዋእለ ሕፃናቶች ወይም ትምህርት ቤቶችን ያካትታል።

የምርምር ዳታዎችን ከእነርሱ ጋር አንካፈልም። *ከጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ጋር ስለሚሠሩት ድርጅቶች ተጨማሪ ለማወቅ [እዚህ](#) ያንብቡ።*

## 7. ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) መቀላቀል ጥቅሞቹ ምንድን ናቸው?

ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) እርስዎንም ሆነ ልጅዎን በቀጥታ ሊጠቅምም ላይጠቅምም ይችላል።

እርስዎ ወይም ልጅዎ ቃለ መጠይቅ ወይም ግምገማ ሲጨርሱ ወዲያውኑ አስተያየት መስጠት እንችላለን። ይህ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል (ክፍል 11ን ይመልከቱ)።

ከጊዜ በኋላ፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በአጠቃላይ ልጆችን እና ወላጆችን በተመለከተ በተለያዩ ሁነኛ ጉዳዮች ላይ ሪፖርት ያደርጋል። ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የብዙ ልጆች እና ወላጆችን ሕይወት ያሻሽላል ብለን ተስፋ እንደርጋለን። ይህንን አጠቃላይ ውጤት ከእርስዎ ጋር እንካፈላለን፣ ይጠቅማሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

## 8. ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) እንዴት ነው የምንቀላቀለው?

የስምምነቱን ቅጽ ሲፈርሙ፣ ለግልዎ የሚሆን ግልባጭ እንሰጥዎታለን። በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በሁሉም ወይም በአንድ አንዶቹ መሳተፍ ይችላሉ። ከተቻለ፣ ሀለቱም ወላጆች ይሳተፋሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። በግልዎ ስምምነትዎን ይሰጣሉ። በተጨማሪ አንድ ወላጅ/አሳዳጊ ለልጅዎ ስምምነቱን ይሰጣል።

## 9. መሳተፍ ይኖርብናል?

በጭራሽ። እርስዎ እንደፈለጉት ነው። ምንም አይነት ውሳኔን ቢወስኑ፣ እርስዎና ልጅዎ የሚያገኙትን እንክብካቤ አይጎዳውም። ይሁን እና፣ ብዙ ሰዎች ቢሳተፉ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።

## 10. ሃሳቤን በኋላ መለውጥ እችላለሁ?

አዎን፣ ሃሳብዎን በማንኛውም ጊዜ መለወጥ ይችላሉ። ይደውሉልን ወይም ኢሜል ያድርጉልን ወይም የጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) ድረገጽ website ይመልከቱ ። ስለውሳኔዎ ምክንያት መስጠት አይጠበቅብዎትም።

- አሁን ስምምነትዎን ቢሰጡም፣ በኋላ መውጣት ይችላሉ። *ስለ መውጣት በተጨማሪ እዚህ ያንብቡ።*
- ስምምነትዎን አሁን ባያደረጉም፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) ሌላ ጊዜ ሊቀላቀሉ ይችላሉ። ይሁንና፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የእርስዎን እና የልጅዎን ቀደምት መረጃዎችን ያጣል። *ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) በኋላ ለመቀላቀል ተጨማሪ እዚህ ያንብቡ።*
- ልጅዎ ሲያደግ (14 እስከ 18 ዓመት ሲሆነው)፣ እንደ አዋቂ ለመሳተፍ እንዲቀጥሉ እድሉ ይኖራቸዋል። *ከጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ጋር ለመቀጠል ተጨማሪ እዚህ ያንብቡ።*

## 11. ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በጤንነታችን ላይ አስተያየት ይሰጣል?

እርስዎ ወይም ልጅዎ ግምገማዎችን ሲጨርሱ፣ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ሊጠቅሙዎት የሚችሉ የውጤቶችን አስታያየት ወዲያኑ ይሰጡዎታል። ይህ አጭር ሪፖርት ሁኔታዎች መስመር እንደያዙ ወይም ስጋት ካለዎት ለምክር ማንን ማየት እንዳለብዎት ያመላክታል። እነዚህን ሪፖርቶች ከሌሎች ጋር መካፈል ይችላሉ፣ ዶክተርዎን ጨምሮ።

ወዲያውኑ ከሚያገኙት አስተያየት ሌላ፣ በግላችን በስተኋላ ከእርስዎም ሆነ ከልጅዎ የተሠሩትን አዳዲስ ወይም የተከማቹ ዳታ ወይም ናሙናዎችን አንፈትሽም። ይህ ማለት ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በስተኋላ የተገኙትን ውጤቶች ለእርሰዎ አይሰጥም።

ይህ በዚህ ምክንያት ነው፡

- በመሰረቱ የምርምር ውጤቶች ለህክምና እንዲሆኑ ሆነው አልተዘጋጁም - ዶክተሮች ህሙማንን ለማከም ሌላ ዓይነት ምርመራዎችን ይጠቀማሉ
- ምርምር የግለሰቦችን ውጤቶች አያይም - የቡድኖችን ብቻ እንጂ
- ከዓመታት በኋላ የሚደረጉ ምርመራዎች ጠቃሚ ወይም ትክክል ላይሆኑ ይችላሉ።

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ወደፊት የስነ ምግባር ፈቃድ በተሰጠው ምርምር እንዲካፈሉ እድሉን ሲሰጥዎት ይችል ይሆናል። ምን አልባትም ተጨማሪ አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ። ለመሳተፍ ሁልጊዜ መምረጥ ይችላሉ።

የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ተመራማሪዎች ግኝቶቻቸውን በስፋትሪፖርት እንዲያደርጉ ያበረታታል - አዲስ እውቀት በሥራ ላይ የሚውለው በዚህ ዓየነት ነው። የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) አጫጭር መግለጫዎችን በድረገጹ ላይ ያደርጋል። ይህ ወላጆችን ይረዳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። የሚታተመው የቡድን ወጤቶች ብቻ ነው - የግለሰብ ውጤት በጭራሽ አይታተምም።

## 12. ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) መቀላቀል ምን ስጋት አለው?

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በምንም ዓይነት የእርስዎም ሆነ የልጅዎን እንክብካቤ ላይ ምንም ጉዳት አያደርስም። ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ግላኝነትዎን ለመጠበቅ ጥብቅ እና ጠንካራ አሰራር አለው። ይህ ማለት የዳታ ግላኝነትን መጣስ በጣም ዝቅተኛ ነው።

የጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) ለመቀላቀል እምነት እንደሚያስፈልግ ይገባናል። እንደእርስዎ ባሉ እምነት ባላቸው ወላጆች ለዛሬዎቹ ልጆችና አዋቂዎች የሚጠቅሙ ለበርካታ ግኝቶች ምሪት ሰጥተዋል። እምነታችሁን ለመካስ አጠንክረን እንሠራለን።

## 13. ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) መረጃችንን በምን ዓይነት ይጠብቅልናል?

የዳታ ስርዓታችን ለጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ብቻ የተዘጋጀ ነው። ፈቃድ ለሌላቸው ሰዎች የጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) ስርዓት ለማግኘት በጣም አዳጋች ነው። እንዲሁም ሕገ ወጥ ነው። መረጃዎችን በጥብቅ በሚያዙበት ቦታ እና በየጊዜው የጥበቃ ፍተሻ በሚደርግባቸው ቦታ እናከማቻለን። በተጨማሪም ሚስጥራዊነትን ለመጠበቅ ለመየለት የሚያስችሉ መረጃዎችን (እንደ ስሞች) ለዳታ ተመራማሪዎች አይገለጥም።

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የግል መረጃዎችዎን (እንደ ስም እና የመገናኛ ዝርዝሮችን) ይጠቀምበታል። ከእርስዎ ጋር ግንኙነታችን የምናቆየው በዚህ ዓይነት ነው።. እንዲሁም፣ ሌሎች የዳታሴቶችን ሥራ ላይ ስናውል (ክፍል 6) መረጃዎቹን ከትክክለኛው ሰው ጋር ለማዛመድ ጥቅም ላይ ይውላል። የግል የአሰባሰብ ማስታወቂያዎችን እና የMCRI's የግለኝነት ፖሲያችንን ማየት ከፈለጉ ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ [www.genv.org.au/privacy](www.genv.org.au/privacy). በግለኝነት ሕግ መሰረት የሰበስብናቸውን እና ያስቀመጥናቸውን የእርስዎን እና የልጅዎን የግል መረጃዎች የማግኘትና የማረም መብት አለዎት። ይህንን ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) በማግኘት ሊያደርጉት ይችላሉ።

እንድናነሳው ካልነገሩን በስተቀር፣ የእርስዎን እና የልጅዎን ዳታ እስከመጨረሻ እናቆየዋለን። ይህ ማለት ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) አዲስ ግኝቶችን ለብዙ ዓመታት ይደግፋል።

የመርዶክ የልጆች ምርምር ኢንስቲቲውት በአውስትራሊያና በቪክቶሪያ የግለኝነት ሕግ የተጠበቀ ነው። የዳታ ጥበቃን፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርአትን፣ ሂደትን እና ፖሊስዎችን በየጊዜው ወቅታዊ እናደርጋለን። ለምርምር ምክንያት፣ የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የምርምር ዳታዎች በሌሎች ሥልጣን ባላቸው ወኪሎች ስርዓት ውስጥ መያዝ ይችላሉ። ይህ ተመሳሳይ የጥንቃቄ እና የግለኝነትደረጃ አለው።

*በተጨማሪ ስለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የደህንነት ዳታ [እዚህ]() ያንብቡ እንዲሁም የግል መረጃዎን ለመቆጣጠር [እዚህ]() ያንብቡ።*

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ለአንድ አንድ መረጃ፣ እንደ ቦታዎች፣ ምስሎች ወይም የጄነቲክ ዳታ ምን አልባትም የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) አካል ለመሆንዎ ይጠቁማል። *በተጨማሪ ሰለ ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) [እዚህ]() ያንብቡ።*

## 14. ተመራማሪዎች ዳታችንን እንዴት ይጠቀሙበታል?

የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ዳታ ጤንነትን ለማሻሻል፣ ለእድገት ወይም ለልጆች እና ለአዋቂዎች ደህንነት ምርምር ላይ ይውላል። በስነምግባር ፈቃድ መሸፈን አለበት። ከጊዜ በኋላ፣ ተመራማሪዎች አዳዲስ እና ጠቃሚ ጥያቄዎችን ለመመለስ በርካታ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ስለዚህ፣ የመረጃዎ ጥቅም ለበርካታ ዓመታት እያደገ ይሄዳል። ሁሉም የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ዳታ በምስጢር ሥራ ላይ ይውላል። ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ዳታውን በሚጠቀሙበት ላይ ሁሉ ጥብቅ ደንብ አለው።

ጥቅም ላይ እንዲውል የመጽደቁ ጉዳይ በሚከተሉት ላይ የተመሰረተ ነው፡

- ጥናቱ ጤና፣ እድገት ወይም ደህንነትን ለማሻሻል ያለመ ነው።
- የቀረበው የዳታ አጠቃቀም የሥነ ምግባር ፈቃድ አለው።
- ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) የአመልካቾችን ደህንነት ፤ ሙያ እና ኢንስቲቲውቱን ወይም ድርጅቱን ይገመግማል።
- ናሙናዎች ወይም ዳታዎች ምስጢር በማይገልጡበት አኳኋን ጥቅም ላይ ይውላሉ - ምክንያቱም የዳታው ተጠቃሚዎች ማነትዎን እንዳያውቁ።
- ተጠቃሚዎች በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ሁኔታዎች ይስማማሉ።

*ስለ ማጽደቅ ተጨማሪ [እዚህ]() ያንብቡ።*

የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ቡድን የእርስዎን ዳታ በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ያደረጉትን ግስጋሴ፣ የጥራትና ምርመራ ዳታሴት ይጠቀምበታል። አንዳንድ ዳታዎች እና ናሙናዎች በአውስትራሊያና በዓለም ዙሪያ ብቻ በሚገኙ ልዩ ላቦራቶሪዎች ይፈተሻሉ። ይህ በምርምር የተለመደ እና ወደ ጠቃሚ ግኝቶች ያመራል። አንድ አንድ ጊዜ ጠቀሜታቸው ከአውስትራሊያ ውጭ ባሉ አገሮችም የሕግ ሽፋን አለው። ይህም በጥብቅ መመሪያ ስር ይካሄዳል፣ ከላይ እንዳሉት ዓይነት የማጽደቅ ደንቦች።

ተመራማሪዎች ዳታ ሲጠቀሙ፣ አብዛኛውን ጊዜ ከላበራቶሪ ምርመራዎች አዳዲስ ዳታ ወይም በአዲስ መንገድ ዳታ በማገናኘት ይፈጥራሉ። እነዚህ በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ተመልሰው ይጨመራሉ። ይህ ጤና ለማሻሻል ተጨማሪ እድል ይፈጥራል።

የንግድ ኩባንያዎች የጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) ዳታ ጤናን ለማሻሻል በሚደረግ ምርምር፣ ለእድገትና ወይም ለደህንነት ለመጠቀም ማመልከት ይችላሉ። ተመሳሳይ የደንቦች ፈቃድ ማሟላት አለባቸው።

አንዳንድ የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ተሳታፊዎች አዳዲስ አቀራረቦችን ለመጠቀም የምርምር ሙከራዎችን ሊቀላቀሉ ይችሉ ይሆናል። ማንኛውም ሙከራ የሥነ ምግባር ፈቃድ ማግኘት አለበት። ማን ለአዲስ አቀራረብ ያመጣል የሚለው በእጣ ይሆናል፣ እንደ ሳንቲምን ወደላይ መወርወር። በአንድ አንድ ሙከራዎች፣ አንድ አንድ ለአዲሱ አቀራረብ የተወሰነላቸው ሰዎች እንዲሳተፉ ይነገራቸዋል። የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ዳታ በመጠቀም የሰዎችን አዲሱን አቀራረብ ማግኘት ወይም አለማግኘቱን ለማወዳደር ጥቅም ላይ ይውላል። የጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ተሳታፊዎች ጥናቶችን መቀላቀል ይችሉ ይሆናል ወይም እንደ የራስ ጉዳቶች ወይም የመስማት መሳን የመሳሰሉትን ልዩ ጉዳዮችን የሚመዘግቡ። ሙከራዎች ወይም ጥናቶች ከጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ጋር ዳታ ለመካፈል፣ ከስነ ምግባር ፈቃድ ጋር፣ ስምምነትዎን ሊጠይቁዎት ይችላሉ። ይህንን እንደግፋለን።

## 15. ተጨማሪ ጥያቄዎች? ማንኛውም ጭንቀት?

ጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) *ድረገጽ* ለብዙ ጥያቄዎች መልሶች አሉት። እንዲሁም ይህ ቃል አለው።

ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) ለማግኘት እባክዎ 1800 436 888 ይደውሉ፣ ወይም በዚህ ኢሜል genv@mcri.edu.au የጻፉልን ወይም በደረገጻችን ይገናኙን website። ሌሎችን ከመርሃግብሩ ጋር ግንኙነት የሌላቸውንም ስለማንኛውም ቅሬታም ሆነ ጥያቆ ፣ እንዴት እንደሚካሄድ ወይም እንደተሳታፊ ስለራስዎም ሆነ ስለልጅዎ መብቶች ማነጋገር ይችላሉ። እባክዎን የምርምር እና የእድገት እና የስነምግባር ዳይሬክተሩን፣ በሜልበርን ሮያል የልጆች ሆስፒታል በስልክ ቁጥር (03) 9345 5044 ወይም በኢሜል rch.ethics@rch.org.au ሊያገኟቸው ይችላሉ።

**በጄነሬሽን ቪክቶሪያ (GenV) ለመሳተፍ ስላሰቡ በጣም አመሰግናለሁ።**
**በእዚህ ጉዞ ጄነሬሽን ቪክቶሪያን (GenV) እንደሚቀላቀሉ ተስፋ አደርጋለሁ።**